# ቃል ኪዳን

ከአብርሃም ዘ-ደብረ ብርሃን

በ5 ፊደላት ተዋቅሮ ከ2 ቃላት የተመሠረተ ጥልቅና ምጡቅ ማህበራዊ ፋይዳ ያለው ሀሣብ ነው ቃል ኪዳን፡፡ አለም ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ አለም ከተፈጠረ በኃላ በፈጣሪና በፍጡር እንዲሁም በፍጡራን መካከል ቃል ኪዳን ነበረ ይላሉ የኃይማኖት ሊቃውንት፡፡ ቃል ኪዳን ማለት አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የሚፈፀም ቃለ መሀላ ሲሆን ውጤቱም በጥብቅ ሥነ- ምግባር የሚመራ ነው፡፡ መልካም ስነ ምግባር ከመልካም ጠባይ ጋር ቁርኝት ያለው ይልቁንም በምንኖርበት ማህበረሠብ እና የአኗኗር ስርአት  ነውር የተባለውን ነገር በመተው ማህበረሠቡ በተስማማበት ጉዳይ ላይ የጋራ መግባባት ፈጥሮ በመኖር የማህበረሰቡን ዕሴቶች ከማክበር ጋር ይያያዛል፡፡ ምንም እንኳን ለመልካም ሥነ-ምግባር አለም አቀፍ ትርጉም ማስቀመጥ የሚከብድ ቢሆንም ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአንድ አካባቢ የሚኖር የህብረተሠብ ክፍል ያከበረውን ማክበር የጠላውን መጥላት ለማህበረሠቡ መልካም ዕሴቶች ተገዥ መሆን የመልካም ሥነ-ምግባር መለኪያ ሊሆን ይችላል ጉዳዩ አከራካሪ ቢሆንም፡
፡

እኛም ስለቃልኪዳን ሥናወራ የተገባውን ቃል በፍፁም ዕምነትና ታማኝነት ለመፈፀም በሚገልጽ ቁርጠኝነት ውስጥ “ **የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ**” ከሚለው አገራዊ ብሂል በመነሳት ነው፡፡ አንድ የአገር መሪ ሲሞት ማልቀስ፣ ሙሾ ማውረድና ለተወሠኑ ጊዜያት የሀዘን ባህል ማድረግ የቀደሙ አባቶቻችን ልማድ እንጅ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ አዲስ ድርጊት አይደለም፡፡ በሀገረ እስራኤል ይልቁንም ከክርስቶስ ልደት በፊት ይህ ድርጊት ጠንካራ መሠረት ነበረው፡፡ ከታላቁ መጽሀፍ እንደምንረዳው ከሆነ የወቅቱ ነገስታት ሲሞቱ በነገስታቱ የአገዛዝ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ዜጎች ለንጉሶቻቸው ባላቸው ፍቅር መጠን ያዝናሉ፣ ያለቅሳሉ፡፡ ከንጉሶቻቸው የመሪነትና የእምነት ጽናት በመነሳትም ለንጉሶቻቸው ያደርጉት ዘንድ የሚገባቸውን ቃል ኪዳን ይፈጽማሉ፡፡ ይህ ልማድ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ዛሬ እኛ ካለንበት ዘመን ደርሷል፡፡ ከክርስቶስ ልደት ወዲህም ቢሆን ይህ አይነቱ ልማድ በእጅጉ ተሠርቶበታል፡፡

ሕዝቡ በህልፈተ ህይወት ለተለየው መሪ ከማልቀስና በተለያዩ መንገዶች ሀዘኑን ከመግለጽ ባሻገር እንደ አገር ለዋለው ውለታ የተለያዩ አይነት መታሠቢያዎችን ማድረግ የተለመደ ነው፡፡ ለምሣሌ የደቡብ ኮሪያ የብር ኖት ለደቡብ ኮሪያ ልማታዊ መንግሥት መሥራችና ለለውጥ መሪያቸው መታሠቢያ ተደርጓል፡፡ የህንድን የብር ኖት ብንመለከት ለነፃነት ታጋያቸው መታሰቢያ አበርክተውታል፡፡ ወደ ልእለ ኃያልዋ አሜሪካ ስናመራም የነፃነት አባቷን መታሰቢያ ያደረገችው  ባዶላር ኖቷ ላይ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ መናገሻ ከተማዋን ለዚሁ ታላቅ ፖለቲካኛ መታሰቢያ አድርጋለች፡፡ እነዚህን አገሮች በምሣሌነት ጠቀስን እንጅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ያላቸውን ተቋማት በስማቸው ከመሠየም አልፈው ሀውልት በማቆም በህይወት የተለዩ መሪዎቻቸውን የመዘከር ልማድ አለማቀፋዊ እንጅ እንግዳ ደራሽ አይደለም፡፡

**ወደ እኛ አገር ስንመጣም በታላቁ መሪያችን በክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ሞት ምክንያት የተነሳው ሕዝባዊ ማዕበል አላማው አላማውን ከመውደድና ከማክበር የመነጨ እንጅ ሌላ**

**አንዳችም ምክንያት የለውም አይኖረውምም፡፡** ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በተፈጥሮ ህግ መሠረት በህይወት ቢለዩንም አገራችን ኢትዮጵያን ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ በዘላቂነትም ወደ በለፀጉት አገሮች የምትገሠግሥበትን ታላቅ ሀሣብና ዘዴውን አሣይተውንና በከፊልም ተግባሩን ጀምረውልን ያለፉ የትግሉ መሪ ናቸው፡፡ በመሪ ድርጅታችን አገር የመለወጥ ቁርጠኛ አመራር አማካይነት የሕዝቡ ቁጭትና ቁርጠኝነት ከታከለበት ያለምንም ጥርጥር የበለፀገች ኢትዮጵያን ዕውን የማድረግ ራዕያቸው ይሳካል፡፡እልህ እና ቁጭት መሬት መንካት የሚችለው በአስተሳሰብና በተግባር የክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴራችንን ፍኖት የሚከተል መሪና ሕዝብ እስከተፈጠረ ድረሰ ብቻ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትራችን፡-

## <u>ከድህነት የሚበልጥ ጠላት የለንም ብለው ያምኑ ነበር</u>

ተገደን የምንገባባቸው ጦርነቶች ብዙ ቢሆኑም ባልሠከነና ጀብደኛ በሆነ አመራር ምክንያት የሚፈጠሩ በርስ በርስ አለመግባባት የሚከሠቱ ጦርነቶች ጥቂት አይደሉም፡፡ ከዚህ አንፃር ሊፈጠሩ የሚችሉ አውደ ውጊየዎችን የማስቆም ዕድላችን በጣም ሠፊ ነው፡፡ ይህንን ስናይ ጦርነት ምንም እንኳን አስከፊ አለም አቀፍ ገጽታ ቢሆንም ልንቆጣጠረው የምንችል በመሆኑ ቁጥር 1 ጠላት ማድረግ ይቸግራል፡፡ በሌላ በኩል ለብዙ አገሮች በጦርነት መተላለቅ ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዬች አንዱ ድህነት ነው፡፡ "ከረሀብ ጦርነት ይሻላል " እንዲሉ እጅና እግርን አጥፎ ከመራብና የበይ ተመልካች ከመሆን ነፍጥ  አንስቶ ብቻውን የሚበላውን የኃይል አሠላለፍ በኃይል በማንበርከክ ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲመጣ ጦርነትን አማራጭ ማድረግ ውጤቱ የከፋ እና ተመራጭ ዘዴ ባይሆንም በብዙ አገሮች ዘንድ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ለዚህም ነው በዜጎች መካከል ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል መዛባት ከተከሠተ ውሎ አድሮ ችግር መፍጠሩ አይቀርም የሚባለው፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ካሣለፉት የ38 ዓመት የትግል ጉዞ የተማሩት መሠረታዊ ጉዳይ ቢኖር ከጦ ርነት አስከፊነት ይልቅ የድህነትን አስከፊነት ነው፡፡ በርግጥ የጦርነት ጥሩ የለውም፡፡ ጦርነት ከሚያስከትለው ሠብአዊና ቁሳዊ ውድመት አኳያ የሚጠይቀው  መስዋዕትነት እጅግ ዘግናኝ በመሆኑ ምክንያት የመጀመሪያ ተመራጭ አይሆንም፤ ይሁን እንጅ ነፃ አገርና ነፃ ሕዝብ ለመፍጠር ሲባል ብዙዎች ጦርነትን እንደ  አማራጭ ተቀብለውት ለውጥ አምጥተውበታል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስተራችንም ከፀረ ዲሞክራሲ የአገዛዝ ሥርዓት ራሳቸውንና የሚመሩትን ሕዝብና አገር ነፃ ለማውጣት የተጠቀሙበት የመጨረሻ አማራጭ ስለሆነ የጦርነትን አስከፊነት ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ይሁን እንጅ በጦርነትም ውስጥ ሆነው የርሀብን አስከፊነት በተጨባጭ የተመለከቱና ዜጎች በድህነትና በርሀብ ሲያልቁ የተመለከቱ ጓድ በመሆናቸው በአንድ ወቅት ተስፋ እስከ መቁረጥ ደርሠውም ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ያለፉ ጓድ በመሆናቸው ከጦርነት ረሀብ እንደሚብስ ለዚህ ደግሞ ድህነትን መዋጋት የሁሉም ዜጋ ድርሻ መሆን እንዳለበት አስምረውበታል፡፡ ለዚህ ነው **ከድህነት የሚበልጥ ጠላት የለንም** የሚለው አረፍተ ነገር ከአንደበታቸው የማይለየው፡፡

## <u>የአንድ  አገር የወደፊት ዕጣ መወሠን ያለበት በአገሪቷና በአገሪቷ ሕዝብ ብቻ ነው የሚል ጽኑ አቋም ነበራቸው</u>

ዜጎች የራሳቸውን ዕጣ በራሳቸው የመወሠን የሙሉ ሥልጣን ባለቤት መሆን አለባቸው፡፡ በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 8 ላይ እንደተጠቀሰው " ይህ ሕገ መንግሥት የኢትዩጵያ ሕዝቦች ብሔር

ብሔረሰቦች የሉአላዊነት መገለጫ ነው ‘’ ይላል እንደ አገር የድርጅታችን ቋንቋ ሕገ መንግሥቱ ነው፡፡ ከሕገ-መንግሥቱ መሠረተ ሀሣብ ውጪ ማንም ይሁን ማን በአገሪችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የመወሠን ስልጣን የለውም፡፡’’ አገር ማለት ሕዝብ ነው ‘’ የሚል ጽኑ አቋም የነበራቸው መሪያችን እያንዳንዱ ዜጋ የራሱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የመወሠን ተፈጥሯዊ አቅምም ስልጣንም አለው የሚል አቋም ያራመዱ የትልቅ ሀሣብ ባለቤት ናቸው፡፡ **ሠው መሆን የሚፈልገውን ለመሆን በሚከፍለው መስዋዕትነት ልክ መሆን የሚፈለገውን ሠው መሆን ይችላል፡፡** ይህ ውሣኔ የራሱ የግለሠቡ እንጅ የማንም ሊሆን አይችልም፡፡ ድሀ መሆን የለብኝም፡፡’’ ማይም መሆን የለብኝም‘’ በሚል ልባዊ ውሣኔ የተነሳ አንድ ህዝብ መሆን የማይፈልገውን ነገር ላለመሆን ተገቢውን መስዋዕትነት ከከፈለ ለምን ድሀ ይሆናል? ለምንስ ማይም ይሆናል? በወደፊት ህይወቱ ላይ የመወሠን ስልጣን ያለው ራሱና ራሱ ብቻ ነው፡፡

ይህንን መሠረተ ሀሣብ እንደ አገርና ሕዝብ ስንወስደውም ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ **የአውሮፖና የሰሜን አሜሪካ የፖለቲካ ፈላስፋዎች በፈለሠፉት የሥርዓተ መንግሥት እና የሥርዓተ ገበያ ፈለግ አንመራም፡፡ መመራት ያለብን ለአገራችንና ለአገራችን ሕዝብ በሚጠቅም የሥርዓተ መንግሥት ፈለግ ነው፡፡ ምክንያቱም የአውሮፖና የሰሜን አሜሪካ ማህበራዊ መሠረተ ከኢትዬጵያ ማህበራዊ መሠረት ፍፁም የተለየ ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ከአገራችንና ከአገራችን ሕዝብ ማህበራዊ መሠረት ጋር የሚስማማ የቅርፀ መንግሥት ፈለግና እና የነፃ ገበያ ሥርዓት መከተል ይኖርብናል በማለት የአገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ መወሠን ያለበን እኛና እኛ ብቻ ነን በሚል ዘመን ተሻጋሪ ፖለቲካዊ ፍልስፍና አገርንና ሕዝብን ከድህነት የማላቀቅ ራዕይ የነበራቸው መሪ ነበሩ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ፡፡**

<u>ዴሞክራሲ የአገራችንና የሕዝባችን የሕልውና ጉዳይ ነው የሚል አቋም ነበራቸው</u>

አለም አቀፍ የሠብአዊ መብት ጥበቃ ተቋማት እንደ እነ Human rights watch እና Amnesty International አይነት ድርጅቶች ስለጠየቁን ወይም በኃይል ሊጭኑብን ስለፈለጉ ሳይሆን ዲሞክራሲ የምንቀበለው ለአገራችንና ለሕዝባችን የሚጠቅም፣ በፅናት የታገልንለት የህልውናችን መሠረት ነው ይሉ ነበር፡፡ እንግዲህ የታላቁ መሪያችንን ሀሣብ በዚህች አጭር ጽሁፍ መቃኘት የሚቻል ባለመሆኑ በዚህ ለመገታት እንገደዳለን፡፡ ይህንን መሠረተ ሀሣብ በአቋም ደረጃ ያራመዱና በአገር አቀፍም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ለዚህ ሕዝብ የወደፊት ህልውና የሚጠቅሙ አጀንዳዎች በማንሳት የታገሉ መሪያችንን አጠናል፡፡ በህልፈተ ህይወት ላጣናቸው መሪያችን የገባነውን ቃልኪዳን መሬት ልናስነካ የምንችለው እኛም፡-

<u>ድህነት ጠል የሆነ የዕለት ተዕለት የአሠራር ሥርዓት መከተል እስከቻልን ድረስ ብቻ ነው፡፡</u>

ድህነትን መጥላት ተፈጥሯዊ ነው ብሎ መግባባት ይቻላል፡፡ ማንም ሠው ድህነትን አይወድም፡፡ ድህነትን ባለመውደድ ብቻ ከድህነት መላቀቅ የሚታሠብ አይሆንም፡፡ ድህነትን የሚጠላ ህዘብ ከድህነት የሚላቀቅበትን መንገድ ቀይሶ ዕቅድን መሠረት ያደረገ የፀረ ድህነት ትግል ርምጃ መውሠድ አለበት፡፡ ሠው የሚጠላውን ነገር በመጥላት ብቻ ከራሱ ህልውና መነጠል የሚችል ፍጡር አይደለም፡፡ የለበስነውን ልብስ ለማውለቅ የምንከተለው ሥርዓት የመኖሩን ያህል ዕድሜ ልካችንን ተብትቦ የያዘንን የድህነት ህይወት ከላያችን ላይ ለማውለቅ በትግል የሚመራ የፍች ሥርዓት መፍጠር፣ ድህነትን የማይቀበል ትዋልድ መገለጫው በበሠለ የሥራ ባህል ተጠምዶ ራሱን ለመለወጥ ዝቅ ብሎ በመሥራት ነው፡፡ ይህንን

ሂደት ተግባራዊ ካላደረግን በፀረ ድህነት ትግሉ የተቀመጠውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማሣካት የሚታሠብ አይሆንም፡፡

ቃላችንን የምንጠብቅ በጠቅላይ ሚኒስትራችን ሞት ምክንያት በተፈጠረው ቁጭት ተነሳሽነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አገሪዊና ሕዝባዊ ራዕይ ስኬታ ስንሠራ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ስናደርግ ነው ራሳችን የለውጥ መሪ በማድረግ የህዳሴ ጉዟችንን ማረጋገጥ የምንችለው፡፡ **አሁን ጠቅላይ ሚኒሰተራችን አርፈዋል፡፡ ያረፉት 38 ዓመት ያለ ዕረፍት በመሥራት ነው፡፡ ያረፉት ከድህነት ጋር በነበራቸው የመረረ ትግል አኩሪ ተጋድሎ በመፈፀም ነው፡፡ ያረፉት ለዴሞክራሲ ባላቸው ጽኑ አቋም አንድ ወጥ የሆነ አገራዊ መግባቢያ ሠነድ/ሕገ-መንግሥት/ በማስረከብ ነው፡፡ ያረፉት ለዘመናት አንገቷን ደፍታ በረሀብና በጦርነት ብቻ ስትታወስ የናረችን አገር ወደ ቀደመ የልዕልና ታሪኳ በመመለስ ላይ እያሉ ነው፡፡ የረፉት ከጐረቤት አገሮች፣ ከአፍሪካውያን ወድሞቻችንና ከአለም አገሮች ጋር ያለንን ጥብቅ ትብብርና የማደግ ፍላጐት ለማረጋገጥ ሌት ተቀን እየደከሙ ነው፡፡ ያረፉት የህዳሴ ጉዟችንን በታላቁ የህዳሴ ግድብና በልዩ ልዩ የመሠረተ ልማት አውታር ዝርጋታ ላይ በማተም ነው፡፡**

ሠው ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል፡፡ ይህ አለምአቀፍ እውነት /universal truth/ ነው፡፡ብዙ የደከሙት ጠቅላይ ሚኒስትራችን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ብዙ ሠርተው አልፈዋል እኛስ? በርግጥ ተወልደን አድገናል፡፡ ከጠቅላይ ሚኒስትራችን የምንለየው እሳቸው የሰሩትን ባለመስራት እና በህይወት ስላለን ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜያችን ሲደርስ በመሞት ሞታቸውን ለመምሰል እንችላለን ፡፡ ከመሞታችን በፊት ግን ያልሠራነው ልንሠራው የሚገባ ሥራ አለን፡፡ በየተሠማራንበት የሥራ መስክ ሁሉ መሥራት ያለብንን ለመሥራት፣ ራስን ለሕዝብና ለሕዝብ ጥቅም አሣልፎ በመስጠት የሚገኝን አገሪዊ ርካታ ለመቀዳጀት፣ በአገር ልማት ውስጥ ዋና ተዋናይ በመሆን ለመጭው ትውልድ የዕድገትና የብልጽግና ቅርስ ለማቆየት ለጠቅላይ ሚኒስትራችን የገባነውን ቃል ኪዳን እንፈጽም፡፡